ለማውጣት እንደመሞከር ነው። ትርፉ መቃጠል ብቻ ነው የሚሆነው። በዱንያ ላይ ተስፋ ማድረጋችንን ስናቆም ብቻ፤ ዱንያ ያልሆነችውንና የሌላትን የጀነት ባህሪ ለሷ መስጠት ስናቆም ብቻ ነው ይህች ዓለም እኛን መስበር ልታቆም የምትችለው።

እንዲሁም አንድ ነገር መገንዘብ አለብን። ምንም ነገር ያለምክንያት የሆነ የለም።ምንም። የልብ መሰበር ሳይቀር ያለምክንያት የሆነ የለም። ህመም እንኳ ሳይቀር ለአንድ አላማ የሚከሰት፤ ለሆነ ምክንያት የሚፈጠር ነው። ያ መሰበር፣ ያ ህመም ለኛ መማርያ እና የሆነ ነገር ምልክት ነው። አንድ የተሳሳተ ነገር እየሆነ እንዳለ እያመላከተን ነው። የሆነ መለወጥ ያለበት ነገር እንዳለ እየጠቆመን ነው። እጃችን በእሣት ሲቃጠል የሚሰማን ህመም እጃችንን ከእሳት ማራቅ እንዳለብን ማስጠንቀቂያ እንደሆነው ሁሉ ውስጣዊ ህመማችን አንድ በውስጣችን ያለን ነገር መቀየር እንዳለብን ማስጠንቀቂያ ነው። የሆነ አላስፈላጊ የሆነ መላቀቅ ያለብን ነገር አለ ማለት ነው። ህመሙ እኛ በሰላሙ ጊዜ መላቀቅ ያልቻልነውን ነገር ሳንወድ በግድ እንድንላቀቀው የተላከ ማስጠንቀቂያ ነው። ለምሳሌ የሆነ ነገር ወደን በተደጋጋሚ እንደምንጎዳው። ያንን ነገር በውዴታ ማቋረጥ ያልቻልን እንደሆነ ህመም ተከትሎት ይመጣል። ዱንያ በጎዳችን ቁጥር ህመሙን እዚያው በዚያው ማስታመም ሳይሆን መራቁና መላቀቁ ነው መፍትሄ የሚሆነው። እንደጎዳችን እያወቅን ልንወዳት አይገባም።

ህመማችን እኛ አጥብቀን የተቆራኘነው ነገር የቱ ጋ እንዳለ ጠቋሚያችን ነው።እንድንናነባ ያደረገንና በጣም ያሰቃየን ነገር የውሸት ተዛምዶ ነው። እነዚያ አላህን ርቀን የተጣበቅንባቸው ነገሮች ናቸው ከአላህ ጋር እንዳንገናኝ በመንገዳችን ገብተው ጋሬጣ የሆኑብን። ህመሙ በራሱ ይህንኑ የውሸት ትስስራችን አመላካች ማስረጃ ነው። ህመማችን እኛ የማንፈልገውና በሕይወታችን ውስጥ መቀየር የምንፈልገውን ነገር መቀየር እንዳለብን እድል ይፈጥርልናል። በርግጥም መቀየር ያለብንን ነገር ስለመቀየር ስናስብ መለኮታዊ መመራት አለን። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوْمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُوا۟ مَا بِأَنفُسِهِمْ﴾

"አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ፀጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ኹኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም።" (አር-ረዕድ ፡ 11)

ከረጅም ዓመታት ተደጋጋሚና ተመሳሳይ ውድቀትና የልብ ስብራት በኋላ በመጨረሻም አንድ ጥልቅ የሆነን ነገር ተረዳሁ። ዱንያን መውደድ ማለት ቁሳዊ ከሆነው ዓለም ጋር በፍቅር መውደቅ መሆኑን በሚገባ ተገነዘብኩ። በርግጥ እኔ ከቁሳዊ ነገራት ጋር የተሳሰርኩ አልነበርኩም። ግና የተጣበቅኩት ከሰዎች፣ ከነገሮች፣ ከስሜቶች ጋር ነበር። ስለሆነም አፍቅሮተ ዱንያ እኔን አይመለከተኝም ብዬ ነበር የማስበው። ግና ልብ ያላልኩት ነገር

በዚህች ዓለም ያጋጠመኝ ህመም ሁሉ መነሻው አንድ እና አንደ ነገር ብቻ መሆኑን ነው... ዱንያን መውደድ።

ይህን እየተረዳሁ ስመጣ ነገሮች ተገለጠልኝ። ችግሬ ምን እንደነበረ መመልከት ጀመርኩ። ችግሬ ይህ ዓለም ያልሆነውን እንዲሆንልኝ መጠበቄ ነበር። ሊሆን የማይችለውን መሻት። ፍጹም እንዲሆንልኝ መመኘት። ይህንኑ አስብ ስለነበረ ይህ ዓለም ጀነት እንዲሆንልኝ በሙሉ ለቅሜ ስታገል ነበር። ጉድለት የሌለበት የጠራና ፍፁም እንዲሆንልኝ። ያሰብኩት እስኪሆንልኝ ድረስ የመታገል ብከነት። ለዚህም ስል ሁሉንም ነገሬን ለመስጠት ዝግጁ ነበርኩ። ይህም ማለት በዙርያዬ ያሉ ሰዎች ጉድለት የሌለባቸው፣ ግንኙነቴ ሁሉ ጉድለት የሌለበት እንዲሆን እመኝ ነበር። ከዚህ ዓለም ሕይወትና በዙርያዬ ካለ ነገር ሁሉ ከፍ ያለን ነገር እፈልግ ነበር፤ ፍፅምናን በመጠበቅ ነበር ሕይወቴን የምገፋው።

በዙርያዬ ያሉ ሰዎች እንከን አልባ እንዲሆኑ እና ግንኙነቴ የተዋጣለት እንዲሆን እጠብቅ ነበር። መጠበቅ መጠበቅ መጠበቅ... ሁሌም መጠበቅ። በዚሁ አጋጣሚ ደስታን ለማጣታችን አንድ ምክንያት መኖሩን እንወቅ። እሱም "መጠበቅ" ነው። በርግጥ እዚህጋ የኔም ከባድ ስህተት አለ። ስህተቴ የነበረው በመጠበቄ ውስጥ አልነበረም፤ እንደ ሰው ተስፋን መቁረጥ የለብንም። ስህተቱ ያለው ጥበቃዬና ተስፋን ያደረግኩት ማን ላይ ነው? በሚለው ነው። ጥበቃዬና ተስፋዬ በፈጣሪዬ ላይ አልነበረም... ከሰዎች ጋር ባለኝ መልካም ግንኙነት ላይ ነበር። ጥበቃዬ በአምላኬ ላይ ከመሆን ይልቅ በዱንያ ላይ ነበር።

እናም በዚህን ጊዜ አንድን ጥልቅ እውነት ተገነዘብኩ። አንድ የቁርአን አንቀፅ አነቃኝ። አእምሮዬ ላይ እየተብላላ ቆየ። የሚገርመው ቀድሞ የሰማሁትና የማውቀው አንቀፅ ነው ዛሬ ያነቃኝ። ደጋግሜ ቀርቼዋለሁ፤ በየሰላቱ የምሰማው አንቀፅ ነው። ነገር ግን ለመጀመርያ ግዜ የሰማሁት ያህል ይህ አንቀጹ ስለኔ እንደሆነ ተገነዘብኩ።

﴿إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا وَرَضُواْ بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَٱطۡمَأَنُّواْ بِهَا وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِنَا غَٰفِلُونَ﴾

«እነዚያ መገናኘታችንን የማይፈሩ ፣ ቅርቢቱንም ሕይወት የወደዱ፣በሷም የረኩ፣ እነዚያ እነሱ ከአንቀፃቻችን ዘንጊዎች የኾኑ» (ዩኑስ : 7)

እዚህ ዓለም ላይ ሁሉም ነገር አለው በሚለው ውስጥ እንጂ፤ ተስፋዬ ጌታዬን በመገናኘት ውስጥ አልነበረም። ተስፋዬ ዱንያ ላይ ነበር። በሷ መተማመን። ተስፋን በዱንያ ላይ ማስቀመጥ ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ነገር ሊቀረፍ የሚችለው እንዴት ነው? ጓደኞች ቢኖራችሁ ጓደኛቻችሁ ባዶነታችሁንና ከፍተታችሁን ሁሉ እንዲሞሉላችሁ አትጠብቁ። ትዳር ስትይዙ የትዳር አጋራችሁ ሁሉንም ነገር እንዲያሟላላችሁ አትፈልጉ። የሥራ

ለው ስትሆኑ ሙሉ ተስፋችሁን በወጤቱ ላይ አታድርጉ። ችግር በሚገጥማችሁ ጊዜ የራሳችሁ ጥንኛ አትሁኑ። በሰዎች ላይ ፈፅሞ ጥገኛ አትሁኑ። በጌታችሁ ተመኩ፤ የሱም ጥንኛ ሁኑ። ይህ ነው ትክክለኛው መፍትሄ- በፈጠረን ላይ ጥገኛ መሆን።

﴿ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ﴾

«አላህ የሁሉም መጠጊያ ነው።» (አል -ኢኽላስ፡ 2)

ችግር የለውም፤ የሰዎችን እገዛና እርዳታ ፈልጉ። ነገር ግን አንድ ነገር ልብ በሉ፤- ሰዎች ፍፁም በሆነ መልኩ ሊያድኗችሁም ሆነ ሊረዷችሁ አይችሉም። አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው እነዚያን ነገሮች ሊያደርግላችሁ የሚችለው። አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው እናንተን መርዳት የሚችለው። እነርሱ የእርዳታ ምንጭ አይደሉም፤ ሊሆኑም አይችሉም። ሰዎች ማድረሻ ሰበብ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) ነገራትን የሚከውንባቸው መንገዶች እንጂ ሌላ አይደሉም። እናንተ የሰው ልጆች ምንም ሆናችሁ ምን የእርዳታም ሆነ ከችግር ነፃ መውጫ ምንጭ አይደላችሁም። አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ እንጂ።... እሱ ብቻ ነው ከችግር መውጫን ፈጣሪ። እኛ ሰዎች የዝንብን መብረሪያ ክንፍ እንኳን መፍጠር አንችልም። ግና ያልሆንነውን ነን ብለን በማሰብ ብዙ ርቀን ተጉዘናል። አላህ (ሱ.ወ.) ነው ነገራትን ከምንም የሚፈጥረው። ቁርአንም ይህን አስረግጦ ነግሮናል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَٱسْتَمِعُوا۟ لَهُۥٓ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَن يَخْلُقُوا۟ ذُبَابًا وَلَوِ ٱجْتَمَعُوا۟ لَهُۥ ۖ وَإِن يَسْلُبْهُمُ ٱلذُّبَابُ شَيْـًٔا لَّا يَسْتَنقِذُوهُ مِنْهُ ۚ ضَعُفَ ٱلطَّالِبُ وَٱلْمَطْلُوبُ ﴾

«እሳንተ ሰዎች ሆይ አስደናቂ ምሳሌ ተገለፀላችሁ፤ ስርሱም አድምጡት፤ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገሏቸው (ጣዖታት) ዝንብን ፈፅሞ አይፈጥሩም። ስርሱ (ስመፍጠር)፤ ቢሰበሰቡም እንኳን፤ (አይችሉም) አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከርሱ አያስጥሉትም፤ ፈላጊውም ተፈላጊውም ደከሙ።»

(አል-ሐጅ ፡ 73)

ከሰዎች ጋር ውጫዊ ግንኙነት ብትፈጥሩም ልቦናችሁን ግን ወደ ጌታችሁ አድርጉ። ከሰዎች ጋር ያላችሁ ግንኙነት አካላዊ ይሁን። ተስፋን በአላህ ላይ ብቻ አሳድሩ።እሱን ብቻ አግኙት። ነብዩላህ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ይህንኑ ባማረ መልኩ ገልጠውታል። እንዲህ በማለት ፡-

﴿ إِنِّى وَجَّهْتُ وَجْهِىَ لِلَّذِى فَطَرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ حَنِيفًا ۖ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴾

«እኔ ስዚያ ሰማያትንና ምድርን ስፈጠረው (አምላክ) ቀጥተኛ ስሆን ፊቴን አዞርኩ፤ እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም።» (አል-አንዓም ፡ 79)

ኑብዩላህ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ወደዚህ ግንዛቤ ከመምጣታቸው በፊት ጨረቃን፣ ፀሐይንና ከዋክብትን ተመልከተው ከጉድለት የጠሩ አለመሆናቸውን ተገንዝበው ነበር። እሳቸው በፈጣሪያቸው ፈታቸውን ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ አዞሩ። እንደ አባታችን ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ያለ መታመን፣ ተስፋ ማድረግና ጥገኝነት በአላህ (ሱ.ወ.) ላይ ብቻ ሊሆን የተገባ ነው።

ያንን ስናደርግ የልብ እርጋታ እና ውስጣዊ ሰላም እናገኛለን። ውስጣችን ዘላቂ ካልሆነው እና ጊዜያዊ ከሆነው ጋር ተጣምሮት ሲፈጥር በተረጋጋ ሁኔታ መገንዘብ ሊኖረን ኢይችልም። ባንድ ወቅት ደስተኛ እንሆናለን፤ ደስተኛ የሆንንበት ምክንያት ሲቀየር ደስታችንም አብሮ ይቀየራል። ከዚያ ሐዘን ውስጥ እንወድቃለን። የደረሰብንን ሁኔታ እንኳ መረዳት ሳንችል ካንዱ ጥግ ወደ ሌላኛው እየተወዛወዝን ስንባክን እንኖራለን። ከዚህ ሁኔታ ጋር እንደተጣበቅንም እንኖራለን።

ታዲያ መጠየቅ አለብን። ተቀያያሪ በሆነው ነገር ላይ ጥገኛ ሆነን ሳለ ተቀያያሪ ያልሆነን ዘውታሪ ደስታ እንዴት ልናገኝ እንችላለን? ፍፁም እርጋታና ዘላቂ የሆነ ውስጣዊ ሰላምን አናገኝም። በስሜት ተቀያያሪነት ውስጥ የምንዘወትረውም ጥገኝነታችን ዘላቂና ቀጣይ በሆነው ነገር ላይ ያላደረግን በመሆኑ ነው።

ጥገኝነታችንና ግንኙነታችንን ዘልአለማዊና ተቀያያሪ ባልሆነው ላይ እስካላደረግን ድረስ የሕይወት ብክነታችን ይቀጥላል። ቋሚ የሆነን ደስታ እንዴት ቋሚ ካልሆነ ነገር ውስጥ እንፈልጋለን። የኸሊፋው አቡበከር ረ.ዐ. ንግግር ይህን ሁኔታ ይበልጥ የሚያብራራልን ነው። የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)ይህችን ዓለም በሞት በተለዩ ጊዜ ባልደረቦቻቸው ራሳቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው፤ ዜና እረፍታቸውንም ማመን አቅቷቸው ነበር።

ማንም ሰው የአቡበከርን (ረ.ዐ.) ያህል የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሊወድ አይችልም። ሆኖም እሳቸው (አቡበከር ረ.ዐ.) አንድ ሰው ጥገኝነቱን እና ተስፋውን በማን ላይ ማሳረፍ እንዳለበት ተገንዝበው ነበር። እናም እንዲህ በማለት ተናገሩ፡-

"ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ.) የሚያመልክ ካለ እወቁ ሙሐመድ አልፏል፤ አላህን የሚያመልክ ግን እወቁ አላህ ዘላለማዊ ነው፤ አይሞትም።"

ያንን ላቅ ያለ ደረጃ ለመጎናፀፍ ከፈለጋችሁ የመሚላት ምንጫችሁን ምንንም ነገር አታድርጉ ከጌታችሁ በስተቀር። አላህን የሕይወት ትርጉማችሁ፣ ምልአታችሁና የደስታችሁ ምንጭ አድርጉ።

﴿إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ اللَّهِ أَتْقَىٰكُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ﴾

«አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤ አላህ ግልፅን አዋቂ ሙስጥንም አዋቂ ነው።» (አል-ሑጁራት ፡ 13)

ይህንን ካደረጋችሁ የማትሰበሩ ነው የምትሆኑት። ድል የምትደረጉም አትሆኑም። ምክንያቱም የተጠጋችሁት ድል የማይደረገውን አምላክ ነውና። ፈፅሞ ባዶነት ሊሰማችሁ አይችልም። መሚላትን ያገኛችሁት ዘላለማዊና እውነት ከሆነው ጌታ ነውና።

የ 17 ዓመት ልጅ ሳለሁ ያየሁትን ህልም ሳስብ ያቺ ልጅ እኔ በሆንኩ ብዬ እገረማለሁ። የገረመኝ ለእሷ የመለስኩት መልስ በራሱ አንድ የሕይወት ትምህርት በመሆኑ ነበር። ሰዎች ለምንድነው የሚለያዩት? ብላ እሷ ለጠየቀችኝ ጥያቄ የመለስኩት መልስ "ምክንያቱም ይህ ሕይወት ፍፁም ስላልሆነ ነው። ቢሆን ኖሮማ ቀጣዩስ ምንድነው ተብሎ ባልተጠየቀ ነበር?" የሚል ነበር።